WIC መድልዎ አያደርግም። እና ኃላፊነቶች

የ WIC ሠራተኛ፡- በቃል ይህ ገጽ ተመልከት።

መብቶቼ

- **የ WIC ምግቦች፡-** ለ WIC ብቁ ከሆንኩ፣ ከዕቃ መግዣ ሱቅ ጤናማ ምግቦችን ለመግዛት የ **WIC** ካርድን አገኛለሁ። WIC ለወር ሙሉ የሚያስፈልገኝን ምግብ ወይም የዱቄት ወተት ሁሉ እንደማይሰጠኝ እረዳለሁ።
- **የምግብ ንጥረ ነገር መረጃ፡-** የምፈልገውን ስለ ምግብ ንጥረ ነገር የሚያወራውን መረጃ አገኛለሁ።
- **የጡት ማጥባት ድጋፍ፡-** WIC በጡት ማጥባት ላይ ድጋፍ በማድረግ ያግዘኛል።
- **የጤና እንክብካቤ መረጃ እና መላኪያዎች፡-** WIC ስለ ሰውነት በሽታን መቋቋም፣ ሃኪም ስለማግኘት፣ እና እኔ ስለምፈልገው ሌሎች አገልግሎቶች እንዳውቅ ያደርገኛል።
- **የጋራ መልካም እርዳታ፡-** WIC እና የሱቅ ሠራተኛ በመልካም እርዳታ እና በአክብሮት በፍትሃዊነት እና በእኩልነት ያስተናግዱኛል።
- **ፍትሃዊ መስተንግዶ፡-** ሕጎቹም ያለ ዘር፣ የቆዳ ቀለም፣ የትውልድ አገር፣ ጾታ፣ የአካል ጉዳት፣ ወይም ዕድሜን መሰረት በማድረግ ልዩነት ሳይኖር ለሁሉም ሰው ተመሳሳይ ናቸው።
- **ፍትሃዊ መሰማት፡-** ለ WIC ብቁ ስለመሆኔ ከውሳኔው ጋር የማልስማማ ከሆነ ለፍትሃዊ መሰማት ልጠይቅ እችላለሁ።
- **የማስተላለፍ መረጃ፡** ወደ ሌላ የ WIC ክሊኒክ ማስተላለፍ እችላለሁ። የማስተላለፍ መረጃን እንዲሰጠን የ WIC ሠራተኛን መጠየቅ እችላለሁ።
- **የግል መብት፡-** መረጃዬ የግል መብቱ የተጠበቀ ነው። በክሊኒኩ ተጽፎ ካልተገለጸ በስተቀር፣ የ WIC ን አገልግሎቶች ለመቀበል WIC መረጃዬን መጠስቀም ይችላል።

ስምምነት

በ WIC ላይ ለመሆን ከእነዚህ ርዕሶች ጋር መስማማት አለብኝ፡

- የ WIC ሠራተኛ መብቶቼን እና ግዴታዎቼን እንዲሁም የ WIC መርኃግብር ሕጎችን ነግሮኛል።
- ለ WIC የሰጠሁት መረጃ በሙሉ እውነት ነው። ማንኛውም ለውጦች ቢኖሩ ወዲያውኑ ለ WIC ሠራተኛ እነግራለሁ።
- የ WIC ሠራተኛ የቤተሰቤን መጠን እና የቤተሰቤን የገቢ ምንጮችን አካቶ መረጃዎቼን በሙሉ ማረጋገጥ ይችላሉ።
- የ WIC ምግቦችን ለማግኘት ከዋሸሁ ወይም እውነታዎቹን ከደበቅሁ፣ ለእነዚያ ምግቦች ዋጋ ለ WIC በጥሬው መልሼ እከፍላለሁ።
- WIC የፌዴራል የድጋፍ መርኃግብር ነው። የ WICን ሕጎች ከጣስኩ፡-
  - የ WIC ሠራተኛ ቤተሰቤን ከWIC መርኃግብር ውስጥ ማስወጣት ይችላል።
  - በመግሥት እና በፌዴራል ሕግ ሥር ባለው በሲቪል ወይም በዓቃቤ ሕግ ወጀል ሥር ሊጠየቅ እችላለሁ።
- የ WIC ን ሕጎችን መጣሴ በምርመራ ከተደረሰብኝ WIC የእኔን መረጃ ለሌሎች ሊያጋራ ይችላል።

በኤሌክትሮኒክስ በመፈረም፣ በሚከተለው ላይ ስምምነቴን እገልጻለሁ፡

- **በዚህ ቅጽ ላይ ያለው ሕጎችን እና ስምምነቶችን አንብቤ፣ ተረድቼ እና ተስማምቻለሁ።**
- **የዚህ ቅጽ ቅጂውን ተቀብያለሁ።**

ተሳታፊዎች/ወላጅ አሳዳጊ/እንክብካቤ ሰጪ ፊርማ ቀን

የተሳታፊ ስም (ሞች)፡- የመጨረሻ ስም፣ የመጀመሪያ ስም

የክሊኒክ ሠራተኛ፡- አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ፣ ለምሳሌ በኮምፒውተር ችግር ጊዜ ወይም መብራት ሲጠፋ ብቻ ተሳታፊ/ወላጅ አስዳጊ/እንክብካቤ ሰጪ በወረቀት ላይ ይፈርማል።

ይሄ ተቋም ሁሉንም ደንበኛ በእኩሌታ የሚመለከት ነው።

Washington State WIC Nutrition Program (የዋሺንግተን የስነምግብ WIC ፕሮግራም) ማንንም አያገልም።

ኃላፊነቶቼቼ

- የ WIC ካርዴን በትክክል እጠቀማለሁ። በሱቅ የ WIC ካርድን ለመጠቀም እና በ WIC የተረጋገጡ ምግቦችን ለመምረጥ መመሪያዎቹን እከተላለሁ።
- በ WIC ላይ ለሚገኝ ሰው ብቻ የ WIC ምግቦችን እና የዱቄት ወተትን እጠቀማለሁ። ለ WIC ክሊኒክ መጠቀም ያልቻልኩትን ምግቦችን እና የዱቀት ወተትን እመልሳለሁ።
- የጠፋ፣ የተሰረቀ፣ ወይም የተበላሸ የ WIC ካርድን ወዲያውኑ ለ WIC ሠራተኛ ሪፖርት አደርጋለሁ።
- የ WIC ካርዴን እና የይለፍ ቁልፌን (PIN) ደኅንነት እጠብቃለሁ። ካርዴን እንዲጠቀም የሚወክለው ማንኛውም ሰው የ WIC ሕጎችን ማወቁን አረጋግጣለሁ።
- WIC እና የሱቅ ሠራተኞችን በመልካም ሁኔታ እና በአክብሮት አስተናግዳለሁ።
- ቀጠሮዬን አከብራለሁ ወይም መድረስ ካልቻልኩ ለ WIC ክሊኒክ እደውላለሁ። ቀጠሮዎቼን ማክበር ካልቻልኩ የሚወስደውን የ WIC የምግብ ጥቅማ ጥቅሞች መጠን ላይ ተጽእኖ ሊያሳድር ይችላል።

የ WIC መርኃግብር ሕጎች

እነዚህ ሕጎች ካልተከተሉ ቤተሰቤ ከ WIC ላይ ሊወጣ ይችላል ወይም ከ WIC መርኃግብር ለወሰድኩት የምግብ ጥቅማ ጥቅሞች መልሼ መክፈል ግዴታ አለብኝ።

- ለ WIC ትክክለኛ እና የተሟላ መረጃ ይስጡ። ይህም ማንነትን፣ የእርግዝና ሁኔታን፣ አድራሻን፣ የቤተሰብ መጠን፣ የቤተሰብ የገቢ ምንጭ እና ለ Medicaid ብቁ መሆንን የሚያሳይ (ProviderOne)፣ Supplemental Nutrition Assistance Program (SNAP፣ የምግብ ንጥረ ነገር ኢጋዥ መርኃግብር)፣ Temporary Assistance to Needy Families (TANF፣ ለችግረኛ ቤተሰቦች ጊዜያዊ ድጋፍ ሰጪ)፣ ወይም Food Distribution Program on Indian Reservations (FDPIR፣ ለሕንድ የተቀመጠ የምግብ ስርጭት መርኃግብርን) ያካትታል።
- በ WIC ካርድ፣ በ WIC ምግቦች ወይም የዱቄት ወተትን ፈጽሞ አይሸጡ ወይም ለመሸጥ አይሞክሩ፣ አይነግዱበት ወይም ለሌላ አይስጡ። ይህም በግል፣ በጽሑፍ፣ በቃል፣ ኦንላይን ወይም በሌሎች ሚዲያ ውስጥ ያካትታል።
- በየወሩ የተፈቀደውን፣ ከ WIC ክሊኒክ በአንድ ጊዜ የ WIC የምግብ ጥቅማ ጥቅሞች መጠን ብቻ ያግኙ።
- የ WIC የምግብ ጥቅማ ጥቅሞች አካል ያልሆኑትን ምግቦች ወይም የዱቄት ወተትን በ WIC ካርድ አይግዙ፣ ወይም ለመግዛት አይሞክሩ።
- በ WIC ካርድ የተገዙትን ምግቦች በገንዘብ፣ በክሬዲት ካርድ፣ የ WIC ምግብ ባልሆነ ወይም የ WIC የምግብ ጥቅማ ጥቅም በሆነው ላይ ከፍተኛ መጠን ባለው ለመለወጥ ወደ ሱቅ አይመልሱ፣ ወይም ለመመለስ አይሞክሩ።
- ክሊኒክን ወይም የመደብር ሠራተኛውን አታንገላታ ወይም አትጉዳ ወይም መደብርን ወይም የ WIC ንብረትን አታውድም።

ስለ WIC ተሳታፊ ሕግ መጣስ እና ቅጣት መጣን በተመለከተ የበለጠ መረጃ ለማግኘት፣
Washington Administrative Code (የዋሽንግተን አስተዳድደር የሥነ ሥርዓት ሕግን) 246-790-530 ይመልከቱ።

http://apps.leg.wa.gov/WAC/default.aspx?cite=246-790-530

WIC መድልዎ አያደርግም።

ከፌደራል የሲቪል መብቶች ሕግ እና የዩናይትድ ስቴትስ የእርሻ መምሪያ [U.S. Department of Agriculture (USDA)] የሲቪል መብቶች ደንቦች እና ፖሊሲዎች ጋር በተያያዘ፣ ይሄ ተቋም በዘር፣ በቆዳ ቀለም፣ በትውልድ አገር፣ በጾታ (በጾታ ማንነት እና በወሲብ አዝማሚያ ጨምሮ)፣ በአካለስንኩልነት፣ በዕድሜ መሰረት አድሎ እንዳያደርጉ ወይም ከዚህ ቀደም ለተሳተፉበት የሲቪል መብቶች እንቅስቃሴ የተነሳ የበቀል ወይም የአፀፋ እርምጃ እንዳያከናውኑ ይከለክላል።

የፕሮግራሙ መረጃዎች ከእንግሊዘኛ ቋንቋ በተጨማሪ በሌሎች ቋንቋዎች እንዲሰጡ ይደረጋሉ። የፕሮግራሙን መረጃ ለማግኘት የተለየ የመግባቢያ ዘዴ የሚያስፈልጋቸው አካለ ስንኩላን ሰዎች (ለምሳሌ እንደ ብሬል፣ በትልቅ ፊደል ሕትመት፣ የድምጽ ቅጂዎች፣ የአሜሪካ የምልክት ቋንቋ)፣ ፕሮግራሙን የሚያስተዳድሩ የግዛት ወይም የአካባቢው ኤንሲዎች ጋር በመሄድ ወይም ደግሞ የ USDA'ን TARGET ማዕከል በ (202) 720-2600 (በድምጽ እና TTY) ደውለው ማግኘት ወይም በፌደራል ሪሌ ሰርቪስ (Federal Relay Service) (800) 877-8339 በኩል USDA ን ደውለው ማግኘት አለባቸው።

በፕሮግራሙ ላይ የተፈጠረ የአድሎ ሁኔታን አቤቱታ ለማቅረብ፣ ቅሬታ አቅራቢዎቹ የ USDA መርህግብር የአድሎ አቤቱታ ማቅረቢያ ቅጽ የሆነው ቅጽ AD-3027 መሙላት አለባቸው፣ ቅጹ ኦንላይን በዚህ አገናኝ፡- https://www.fns.usda.gov/sites/default/files/resource-files/ad3027-amharic.pdf ፣ ወይም ከማንኛውም የ USDA ቢሮ፣ በ (866) 632-9992 ላይ በመደወል፣ ለ USDA የሚላክምደብዳቤ በመፃፍ ማግኘት ይችላል። ደብዳቤው የአቤቱታ አቅራቢውን ስም፣ አድራሻ፣ ስልክ ቁጥር፣ እና ተፈጽሟልምየተባለውን የሲቪል መብቶች ጥሰት ሁኔታ እና ቀን፣ ጉዳዩን የሚመለከተውን የሲቪል መብቶች ምክትል ሴክረታሪ [Assistant Secretary for Civil Rights (ASCR)] መጥቀስ፣ ተፈጽሟል የተባለውን የአድሎ አሰራር በቂ በሆነም ሁኔታ በዝርዝር ማስፈር አለበት። የተሞላው የ AD-3027 ቅጽ ወይም ደብዳቤ ለ USDA በሚከተለው አድራሻ መቅረብም አለበት፡-

- በደብዳቤ፡- U.S. Department of Agriculture
  Office of the Assistant Secretary for Civil Rights
  1400 Independence Avenue, SW
  Washington, D.C. 20250-9410;
- ፋክስ፡- (833) 256-1665 ወይም (202) 690-7442፤ ወይም
- ኢሜይል፡- program.intake@usda.gov

Washington State Department of HEALTH

DOH 962-987 September 2026 Amharic

ይህን ሰነድ በሌላ ቅርጸት ለማግኘት፣ ወደ 1-800-841-1410 ይደውሉ። መስማት የተሳናቸው ወይም መስማት የሚቸግራቸው ደንበኞች ወደ 711 (Washington Relay) መደወል ወይም ወደ WIC@doh.wa.gov ኢሜይል ማድረግ ይችላሉ።